ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## የዐርባ ሦስት ዓመት ጎልማሳ

## ዓላማውን ሳይረሳ !

የሚያዝያ ወር ፓርቲው የተመሰረተበት ወር ነው ። ዐርባ ሦስት ዓመት ሆነው። ይህ በዘመን ቀመር ሲሰላ፤ የአንድ ትውልድ ዕድሜ መሆኑ ነው። በቀላሉ የሚታይ ዘመን አይደለም ። የዘመናት መቁጠርን ስሌት እየመዘገቡ መኖር ብቻ አርኪ ነው ከተባለ ፤ ኢትዮጵያ፤ ታሪኳን በሺዎች ከሚቆጠሩ ዘመናት ጋር ማጣቀስ የምትችል ሀገር ነች።

ይህ የሚያረካን ከሆነ ደግሞ ፤ የረዥም ዘመን ዕድሜና የበለፀገ ታሪክ ባለቤቶች የሆን ሕዝቦች ነን ። በዚህ ረገድ የሚስተካከሉን ሀገሮች ቁጥር ትንሽ ይሆናል ። ህንድንና ቻይናን ለዐብነት መጥቀስ ይበቃ ይሆናል። ግን እነርሱ በሥልጣኔ እጅግ ጥለውን ሄደዋል ። የእነርሱ ምጥቀትና የእኛ ባለንበት መርገጥ ምክንያት ሊበዛ ቢችልም፤ ወደ ኋላ ለመቅረታችን ግን፤ ምክንያቶችን እንደ ማጠየቂያ እያደረግን መኖር አንችልም ።

" በሉ እናንተ ምጠቁ እኔ እንዳለሁ አለሁ፤

ችግር ተሸካሚ ባለ ዕዳ ሆኛለሁ፤

በጥንቱ ኑሮየ ኑሮን እገፋለሁ፤

ችግሬን አስወጋጅ ጀግና እፈልጋለሁ። "

ያለችውን ጥሪ በመቀበል ነበር ፤ የዛሬ ዐርባ ዓመት ኢሕአፓ የተመሰረተው ። ለዚህ ሕዝባዊና ታሪካዊ ጥሪ ፤ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ተደራጅቶ መቅረብ ወቅታዊና አንገብጋቢ ስለነበር ፤ ፓርቲው ተደራጅቶ፤ ለትግል መሥዋዕት ራሱን ማዘጋጀቱን ለሕዝብ አበሰረ። ፓርቲው በተወለደበት አካባቢ ሀገራችን የነበረችበት ሁኔታ፤ ከሞላ-ጎደል፤ ይህንን ይመስል እንደነበር የትላንቱ መራራ ትዝታ ነው ።

1ኛ. ኢትዮጵያ በፍፁም አምባገነናዊ የዘውድ አገዛዝ ስር ነበረች።የዴሞክራሲ መብቶች አልነበሩም። የመናገር ፤ የመጻፍ የመሰብሰብና ኃሳብን በአደባባይ በነፃ የመግለፅ መብቶች የተዳፈኑ ነበሩ።

2ኛ የዜጎች ዕኩለነት አልነበረም ። ሕዝቡ በድህነት፤ በህመምና በርሃብ፤ በበሽታ በብዛት ያልቅ ነበር።

3ኛ የትምህርት ዕድል ለሀገሪቱ ህጻናት ለሁሉም ባለመዳረሱ፤ ማይምነት በሚያስፈራ ደርጃ አጥልቅልቋት ነበር።

4ኛ. የዳኝነትና የፍትህ ዕጦት ዜጎችን አስመርሮ ነበር። የሕዝብ ተቆርቋሪዎች በሙሉ ያልፍርድ ወኅኔ ቤት ይታሰሩ ነበር።

5ኛ. የሀገሪቱ ለም መሬት በጥቂቶቹ የመሬት ከበርቴዎች እጅ ስለነበር፤ የመሬት ላራሹ ጩኸት በየቦታው ያስተጋባ ነበር ። ተጠማኙ ገበሬ፤ ለባለርስቶች የሚከፍለው ግብር መጠን አልነበረውም ። መሬት፤ በአገዛዙ ቁጥጥር እንጅ ለሕዝብ አልሆነም ። የመሬት ጥያቄ፤ አሁንም ገና ምላሽ አላገኘም ።

6ኛ. ከሀገሪቱ እንገንጣል ባዮች፤ በሰሜን፤ በምዕራብና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መሳሪያ ታጥቀው በመነሳት የሀገራችንን ህልውና ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥለውት ነበር ። ይህም በበኩሉ የሀገራችን ነጻነትና ሉዓላዊነት ለባዕዳን ኃይሎችና ለእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ዳርጓት ነበረ።

7ኛ. ሁሉም ችግሮች ተደማምረው፤ ሀገራችንን ከመኖር ወደ አለመኖርና ወደ መጨረሻ የጥፋት አፋፍ አድርሰዋት ነበር።

ከዛሬ አርባ ሦስት ዓመት በፊት የነበረው የሀገራችን ሁኔታ፤ እንግዲህ፤ ከሞላ-ጎደል፤ ይህንን ይመስል ነበር። ይህንን ኢትዮጵያ የወደቀችበትን አደገኛ ሁኔታ ከልብ የተረዱ ሀገር ወዳድ ተራማጅ ኢትዮጵውያን፤ የነበራቸው ምርጫ ሁለት ብቻ ነበር ።

አንደኛው፤ እጅ-እግር አጣጥፎ በመቀመጥ፤ የሀገሪቱን መጨረሻ ዳር ሆኖ መመልከት፤ ሁለተኛው ደግሞ ተደራጅቶ ሀገሪቱን ከተቃጣባት የመጥፋት አደጋ ፈጥኖ ማዳን ነበር። ፓርቲውን የመሠረቱት ኢቲዮጵያውያን ኃይሎች የመረጡት ሁለተኛውን ነበር ። በዚህ የሁኔታ አስገዳጅነትና ሀገራዊ- ታሪካዊ ጥሪን መሠረት አድርጎ የተፈጠረው ፓርቲ፤ ዓላማውን ሳያጥፍ ለአርባ ሦስት ዓመታት በፅናት በመታገል ላይ ይገኛል ። ገና ከመነሻው ሁለት ባላንጣዎች ገጥመውት ነበር ። እነርሱም፡--

1ኛ  የኢትዮጵያን ኅልውና የማይፈልጉ ባዕዳን ኃይሎችና  2ኛ. ተገንጣይ ክፍሎች ናቸው ። ሁለቱም፤ ፓርቲውን እንደ ደመኛቸው ቆጠረውት  ልዩ ልዩ ደንቃራዎች ፈጥረውብታል ። የየራሳቸው ምክንያቶች ነበሯቸው፡፤ አሁንም አሏቸው። ባዕዳን ኃይሎች፤ ሀገር -ወዳድ ኃይልም ሆነ መንግሥት በማነኛው ሀገር እንዲበቅል አይፈልጉም ። የዚህም ምክንያት፤ ጥቅማቸውን የሚጻረርባቸው ሆኖ ስለሚያገኙት ብቻ ነው።

ኢሕአፓን ከመጀመሪያው ጀምረው በሀገር ወዳድነቱ  ስለፈረጁት፤ መክኖ እንዲቀር እንጅ፤ ፋፎቶ እንዲያድግ አልፈለጉም።  አሁንም አይፈልጉም።  በዚህ በኩል ዕውነት ነበራቸው። አሁንም  አላቸው። የባዕዳንን ርዳታ ለማግኘት ሲል በሀገራዊ ጥቅም ላይ ስለማይደራደር፤ የዕነርሱ ርዳታና ትብብር በአፍንጫ ይውጣ ብሎ በመወሰኑ፤ እንደ ዘላቂ ጠላት አድርገው  ወሰዱት ። መጥፋት አለበትም ብለው ደመደሙ ።

የጎረቤት ሀገራትም እንደዚሁ ፤ ፓርቲውን የጥቅማቸው ተቀናቃኝ  አድረገው  ስላዩት፤ ለዕድገቱ ጋሬጣዎች ነበሩ። ሱድኖች፤ የኢትዮጵያን ወሰን  ጥሶ በመግባት ዛፍ   እየቆረጡ መሄዳቸውንና የሱዳን ገበሬዎችም በሀገራችን መሬት ላይ ማረሳቸውን ተቃውሞ ከልክሏቸዋል ። በዚህ ብዙ ጥቃት ደርሶበታል  ።

የሱማሊያ ሪፑብሊክ መሪዎች፤ ኦጋዴንን ቆርጦ ለመውሰድ ያደረጉትን ፍላጎት በግልፅ በመቃወሙ፤ ጥቃት ደርሶበታል። ፓርቲው፤  በኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም ማስከበርና  መከላከል ላይ እጅግ ቀናዒ መሆኑን የተገነዘቡ ሁሉ  ተረባርበውበታል።

2ኛ.  ተገንጣዮችና አስገንጣዮችም ፤ ፓርቲው ዓላማቸውን  ስለተቃወማቸው፤ በበኩላቸው፤ ተባብረው አጥቅተውታል ። ሻዕቢያና ወያኔ፤ ኢትዮጵያን ለመከፋፍል ያቀዱትን ሴራ አስቀድሞ  በማወቁና በመቃወሙ  ፤ በደመኝነት ፈርጀው በአንድ ላይ ተሰልፈውበታል ። ኢሕአፓን ፤ የታላቋ ኢትዮጵያ ( ዐባይ ኢትዮጵያ ) አቀንቃኝ ትምክህተኛ እያሉ ተሳልቀውበታል ። ይህ ስላቅ ግን ፓርቲውን ያኮራዋል እንጅ  አላሸማቀቀውም ። አስቀድሞ ተገንጣዮችንና አስገንጣዮችን በመቃወሙም፤ አኩሪ ታሪኩን ደጓሳ አድርጎታል ። ፓርቲው ከተመሰረተ ጀምሮ፤ መነሻው፤ መገስገሻውና መዳረሻው ኢትዮጵያዊ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ  ባደረገው መከላከልና  በያዘውም የማያወላውል  አቋም ምክንያት ፤ ከኢትዮጵያ ጠላቶች በኩል ያልተቋረጠ ጥቃት ቢደርስበት ሊያስደንቅ አይችልም።  በሀገር ጥቅም ላይ የሚወሰድ አቋም ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን  አስቀድሞ  ተረድቶ  ነው ትግሉን  የጀመረውና !

ሌላው ለመውሰድ ያልደፈረውን፤ ሀገራዊ አቋምና ውሳኔ መውሰድ፤ የሚያስከፍለውን ከባድ መሥዋዕት አበክሮ በመረዳቱ ፤ ፓርቲው በተደጋጋሚ ያጋጠመውን አስቸጋሪ አደጋና ጥቃት እንዳመጣጡ ለመመከት አስችሎታል ። ይህም ለቀራጡ ኢትዮጵያዊ ባኅርዩ መረጋገጫ ሆኖታል ።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፤ በዘመናት መለዋወጥ ፤ በመንግሥታት መቀያየርና በሥርዓት መገለባበጥ፤ መሠረቱ የሚናጋ አይሆንም። የፓርቲው ኢትዮጵያዊነትም፤ በዚህ መሠረታዊ ዘለዓለማዊነት ዙሪያ የሚሽከረከር ሃቅ ነው። የማያቋርጥ ህልውና በመሆኑም፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል ። የዛሬ ዐርባ ሦስት ዓመት ትግሉን የጀመረው ትውልድም፤ ኢትዮጵያዊነት፤ ሳይሸረፍና ሳይቆራረስ፤ በምልዑነት ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ፤ ኃላፊነቱ እንደሆነ ያምናል ።ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚፍጨረጨሩ ሁሉ፤ እነርሱ ይጠፏታል እንጅ ሀገራችን አትጠፋም ። ፈፅሞ ! ይህ ሀቅ በታሪኳ ተደጋግሞ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

በዐርባ ሦስት ዓመታት ውስጥ ሦስት ሥርዓቶች ከተለዋወጡ በኋላ፤ ኢትዮጵያ የት ደርሳለች ? የሕዝቡ የወደፊት ዕጣ ፈንታስ ምን ሊሆን ይችላል ? የሚለው ቆጥቋጭና አቅጣጫም አመልካች ጥያቄ ፤ ሁል ጊዜ አዕምሯችንን ዕረፍት ይነሰዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለዴሞክራሲ ፤ ለፍትኀ-ርትዕ ፤ ለመልካም አስተዳደርና ለብልፅግና ሲል መከፈል ከሚገባው በላይ ፤ የህይወትና የንብረት ዋጋ ለአለፉት ዐርባ ዓመቶች መክፈሉ የተመዘገበ ነው። ያ ሁሉ ከባድ መሥዋዕት ተከፍሎ ግን፤ ሀገራችን አሁን በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች ? መልሱን የሚከተሉት ነባራዊ ሁኔታዎች ይመልሱታል ።

- የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ተጨራምቷል ። የባኅር ወደቧን አጥታለች ። ኤርትራውያን ልጆቿ/ወገኖቿ እንዲገነጠሉ ተደርገዋል።
- ሰፊው የምዕራቡ መሬቷ ለባዕድ መንግሥት ተሰጥቷል። በአራቱም ማዕዘናት ያሉት ወሰኖቿ ተደፍረዋል ።
- ሰፋፊና ለም መሬቶቿ የባዕዳን ከበርቴዎች መጠቀሚያ ሆነዋል ። ዜጎቿ ግን ከትውልድ ቦታቸው ተፈናቅለዋል/ተነቅለዋል። ተባርረዋል ።
- ማዕደናትና፤ የከርሰ- ምድር ሀብቷ ፤ በውጭ ባለሀብቶች እየተመዘበረ ነው። ባለቤትና ተቆርቋሪ በማጣቷ፤ የማንም አልፎ-ሂጅ መጠቀሚያ ሆናለች ።

- የሀገሪቱ ቆዳ ስፋት የተቀነሰ መሆኑ ባያከራክርም፤ የሕዝቧ ቁጥር ግን የዛሬ ዐርባ ሦስት ዓመት ከነበረው በሦስት ዕጥፍ ጨምሮ፤ በአሁኑ ጊዜ ቁጥሩ ከዘጠና ሚሊዮን በላይ ሆኗል። ለዚህ ዜጋ አገልግሎት የሚሆን፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ ፤ የማኅበራዊና የጤና ሥር ዓት አለተዘጋጀለትም። መሠረተ-ልማትና አገልግሎት የረባ ድርሻ የላቸውም ።

- በዘር ላይ የተመሠረተ የአንድ ጎሳ አምባገነናዊ አገዛዝ፤ መላውን ሕዝብ ሰንገ በመያዝ መፈናፈኛ አሳጥታል ። የዴሞክራሲ መብቶች፤ የፍትኅ ርትዕና የህግ የበላይነት ደብዛቸው ጠፍቷል። አንድ - ለአምስት በሚባል ጠርናፊ ተከታታይ የስለላ መረብ፤ የእያንዳንዱን ዜጋ መውጫ መግቢያ ይቆጣጠራል ።

- ሁሉም ዜጋ ፤ሀገሩ የምድር ሲዖል ስለሆነችበት ወንድ ሴት፤ ጎጻን ሽማግሌ፤ ከተሜ ገጠሬ ፤ ቄስ መነኩሴ፤ ሸህ -ፋቅራ፤ የተማረ ያልተማረ ሳይል፤ ሀገሩን እየተው በብዛት ይሰደዳል ። መዳረሻውን ግን አያውቀውም ። በአሁኑ ጊዜ፤ በዓለም ዙሪያ፤ የኢትዮጵያ ሰደተኛ የሌለበት ሀገር አይገኝም ።

- በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሠረተ አምባገነን አገዛዝ ሕዝቡን እየከፋፈለ፤ የሀገሪቱንም ኅልውና ወደ አደገኛ የጥፋት ጠርዝ / ፀድፍ እየገፋት ይገኛል ።

- አክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ :---- ፖቨርቲ ኤንድ ሂውማን ደቨሎፐመንት ኢኒሽቲቭ ( ድህነትና የሕዝብ ዕድገት ) Oxford University : ---- ( Poverty and Human Development Initiative 2014/ 2015 / Index Data Base ) በሚል ርዕስ በ 2014/ 2015 ባወጣው ዓመታዊ ዘገባ ፤ ኢትዮጵያን በዓለም ደሃ አገሮች ከመጨረሻው ሁለተኛ ርከን መዝግቧታል ። ከኢትዮጵያ በታች ያለችው ኒጀር ነች ። ከዐርባ ሦስት ዓመት በኋላ፤ ዛሬም ሀገራችን፤ከድኅነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቃ ያለች መሆኗን ያረጋግጣል ። በቀን ሦስት ጊዜ መብላት ቀርቶ፤ ለአንድ ጊዜ እንኳን የሚላስ የሚቀመስ የሌላት ሀገር ነች:: ከዐርባ ሦስት ዓመት በኋላ ያለችው ኢትዮጵያ ይህች ናት ! ይህንን ትመስላለች !

ከላይ የተዘረዘሩት ሀቆች፤ ከዐርባ ሦስት ዓመት በኋላ፤ ኢትዮጵያ እንዴት ነች? የትስ ደርሰናል? ለሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጡናል ። ይህንን የሀገራችንን ተጨባጭና ነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ ከቻልን፤ ምን ማደረግ ሊኖርብን ነው ? አቅጣቻችንስ እንዴት መቀየስ

አለብን?  ለተባሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልሶች መስጠት ያስፈልጋል  ። የችግራችንን መፍትሄ ለመፈለግ፤ ሀገሪቱ ያሳለፈቻቸውን ውጣ ውረድ በጥሞና ሁሉም ዜጋ ገምግሞና  መርምሮ አንድ ዓይነት ግንዛቤ ሊደርስ ግድ ነው።

አሁን ሀገሪቱን የተጫናት ሥርዓት ክፉ ጠላት ነው። ለከፋ ጠላት፤ የከፋ ትግል ያስፈልጋል ። ዘረኛ አገዛዝ ጨካኝ ነው።  ጨካኝ ሥርዓትን ለመለወጥ ደግሞ፤  ጨክኖ መታገልን ይጠይቃል ። የጀርመን ናዚዎች፤ የኢጣሊያ ፋሽስቶች፤ የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ዘረኞች ሁሉ፤ ጨካኞች ነበሩ።  ሁሉም የተወገዱት፤  መራራ መሥዋዕትን በጠየቀ  ጠንካራ  ትግል ነበር ።  የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ትግሉን በድል ለማጠናቀቅ  ካስፈለገው፤ ጨክኖ መነሳት አለበት ።ረሀብና ጥማትን፤ በልመና ፤ ዕለታዊ   ችግርንም ምናልባት  በምፅዋዕት   ማስታገስ ይቻል ይሆን ይሆናል። ግን ዘላቂ መፍተሄ አያመጥም ።  ነጻነትን ያህል ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ጸጋ ለማግኘት ፤ ከፍተኛ ዋጋን የሚጠይቅ መሥዋዕት ከመክፈል  ውጭ ሌላ ምርጫ አይኖርም ።

የምዕራባውያን ርዳታ ፤  የዓለም  አቀፍ  ኅብረተስብ  ሀዘኔታ ፤  የሰብዓዊ  መብቶች ተቆርቋሪ ድርጅቶች ዕሪታ፤  የኢትዮጵያን ሕዝብ መከራ አላቃለሉለትም ።  ከእነርሱ የሚጠበቀው የትም አላደረሰንም።  በእነርሱ ማመካኘትም ፋይዳ የለውም። የችግራችን  ምንጩ በአመዛኙ፤ የእኛው የውስጣችን  ጉዳይ ስለሆነ፤ ለመሠረታዊ መፍተሄ ፈላጊዎችም እኛው ራሳችን ብቻ ነን  ።  የዚህ ዐብነቱ ደግሞ ፤ የሁሉም መስማማት ነው። ሁሉም ኃላፊነቱንና ግዴታውን  ሳይወጣ  እየቀረ፤ በሌላው  ላይ  ጣት  ቢጠቋቁም፤  ለችግሩ  መባባስ  እንጅ፤  ለመፍተሄው  ፍለጋ  ቅንጣት የሚያበረክተው ፋይዳ የለውም  ። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዐርባ ሦስት  ዓመታት በኋላ፤ አሁንም ፤

" ተሸካሚ  ሆንኩኝ መከራና ጣጣ

  ችግሬን አስወጋጅ  ወዴት ሄጄ ላምጣ ? "  እያለች ነው።

አሁንም፤ እኛ የሀገራችንን  ችግር፤ ለማስወገድ ትግላችንን አምርረን  እንቀጥላለን ። በዐርባ ሦስት ዓመታት የትግል ቃል-ኪዳን ጠብቆ መቀጠሉንም እንኮራበታለን ።  እንቀጥልበታልን ! ሁሉም ልዩነቱን እያሸጋሸገ ተበብሮ ሀገሩን ከጥፋት እንዲያድን ጥሪ እናደርጋለን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !